# ስለ ስቅለት እስላማዊ ብዥታዎች

## ለየሕያ የድምፅ መልስ የተሰጠ መልስ

[www.ewnetlehulu.org](http://www.ewnetlehulu.org)

የየሕያን የሰሞኑን ሁኔታ ስመለከት ጀነትን ያየ ጂሃዳዊ ወደ ምድር ተመልሶ እንደገና መገደል እንደሚፈልግ፣ አሁንም ተመልሶ እንደገና መገደል እንደሚፈልግ መሐመድ የተናገረው ሐዲስ ትዝ አለኝ፡፡ (ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 4፣ መጽሐፍ 52፣ ቁጥር 53)

ይህ ወገናችን ሰሞኑን ለጻፍኩለት የመጽሐፍ ሒስ የሰጠውን ለ40 ደቂቃ አንድ ከሩብ የቀረው የኦዲዮ ምላሽ ወዳጄ ልኮልኝ አደመጥኩት፡፡ የመጀመርያዎቹን አምስት ምላሾቼን ለማስተባበል የሞከረ ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ በሌላ ቦታ መልስ የተሰጠባቸውን ሙግቶች መልሶ ይጠቀማል፡፡ ይህም ሙሉውን ጽሑፍ አለማንበቡን፤ ሲከፋም አንብቦ ሳለ የትጥቅ እጥረት ስለገጠመው እነዚያኑ የከሸፉ ሙግቶች ለመተኮስ መገደዱን አመላካች ነው፡፡ ይህ ተግባሩም ፈረንጆች “paint oneself into a corner” የሚሉት ዓይነት ነው፤ ከበር ጀምራችሁ ወደ ውስጥ እስከ አንዱ ጠርዝ ቀለም ቀብታችሁ መውጫ ሲጠፋችሁ እንደማለት ነው፡፡ ጉዳዩ “ካፈርኩ አይመልሰኝ” ዓይነት ሆኖበት እንጂ የመልስ ምቱ ከአቅሙ በላይ እንደሚሆንበት ዘንግቶት አይመስለኝም፡፡ የኩረጃ ጉዱ መጋለጡ ቢያስደነብረውም ዝም ከማለት ይልቅ መልስ መስጠት የደረሰበትን የሞራልና የስብዕና ኪሳራ እንደሚቀንስለት ያሰላ ይመስላል፤ የተሳሳተ ስሌት ሆነ እንጂ፡፡ ለዚህም ይመስላል “ዝም ካልን መልስ የላቸውም እንባላለን” በሚል መነሻ ምላሽ መጻፋችንን ደጋግሞ የሚናገረው፡፡ ይህም የግሉን ሥነ ልቦና የሚያንፀባርቅ ሲሆን በሕክምናው ዓለም “Psychological projection” ይሰኛል፡፡ ይህም ሰዎች “አንተ እንዲህ እያሰብክ ነው፣ እንዲህ እየተሰማህ ነው፣ ወዘተ.” በማለት ደጋግመው በመናገር ሳይታወቃቸው የገዛ ስሜታቸውን የሌላው በማስመሰል የሚናገሩበት ሁኔታ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ስሜቱ ጣታቸውን የሚቀስሩበት ሰው ሳይሆን የራሳቸው ነው፤ ይህም እያስተናገዱ የሚገኙትን ሁኔታ መሸከም ያለመቻላቸውና የደካማነታቸው ምልክት ነው፡፡ የሕያ “እችላለሁ” ብሎ መጽሐፍ ጽፏል፤ መጽሐፍ ከጻፈ ደግሞ መልስ ሊሰጠው እንደሚችል ማሰብና መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እንኳንስ እርሱ ጀማሪ የሆነ ጸሐፊ ይቅርና የበሰሉ ሊቃውንት እንኳ ለመጻሕፍታቸው መልስ ይጻፋል፡፡ ታድያ የሰፈራችን ልጅ የሕያ ማነውና ነው መልስ የማይጻፍለት? እንደው ምን ዓይነት ቦምብ የሆነ ሙግት ይዞ ብቅ ቢል ነው ሙግቱ አይነኬ የሚሆነው? ማሕበራዊ ሚድያ ላይ ሆይ ሆይታ ስለበዛለት ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሰ መስሎት ይሆን? በፊደል ግድፈቶችና በሌሎች ብዙ ችግሮች ለተተረማመሰችው ሚጢጢ መጽሐፉ ዕውቅናን በመስጠታችንና የአደባባይ የውይይት ርዕስ እንድትሆን በማድረጋችን ኩራት ሊሰማው በተገባ ነበር፡፡ ዳሩ ግን የሰው ሥራን የመስረቅ ወንጀል በመፈፀሙና በመጋለጡ ምክንያት እንደ መልካም ዕድል ከመቁጠር ይልቅ መደንገጡ የሚጠበቅ ነው፡፡

ይህ ወገናችን ከስሜታዊነት የጸዳ አስተውሎት የበላይነት ባለው የጽሑፍ ዓለም የእርሱ ሙግቶች ቦታ እንደሌላቸው ስለተገነዘበ ስሜታዊነትን ለመቀላቀልና የሞጋቹን ሙግቶች በተሳሳተ መንገድ ለማቅረብ ምቹ እንደሆነ ባሰበው የድምፅ መልእክት ምላሹ ሰጥቷል፡፡ ያቀረበው ምክንያት ደግሞ "ጊዜ ለመቆጠብና የሞጋቹን ሙግት ንቄ" የሚል የሰነፍ ሰበብ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ አንባቢያን ቀደም ሲል ለመጽሐፉ የተሰጠውን ምላሽ እንዳነበቡና የየሕያን የኦዲዮ ምላሽ እንዳደመጡ ቅድመ ግንዛቤ በመያዝ ወደ መልሴ እገባለሁ፡፡ (የመጀመርያውን ምላሽ ለማውረድ **እዚህ ጋ** ጠቅ ያድርጉ)

--------------------------------------------------------------------------------

1. የሕያ ተሰደብኩ ተዘለፍኩ ዓይነት ስሞታዎችን በማቅረብ አድማጮቹ ስለ እርሱ የኀዘኔታ ስሜት እንዲኖራቸው ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ለየሕያ የማላዝንባቸውና ግሳፄው ተገቢ እንደሆነ የማምንባቸው ግልፅና አሳማኝ ምክንያቶች አሉኝ፡፡
    - የሕያ የሰው ሥራ ሙቶ በሙቶ በመገልበጥ የራሱ ሥራ አስመስሎ አቅርቧል፡፡ እርሱ ዐይኑን በጨው አጥቦ ቢክድም እያንዳንዱ ነገር ከጠቀስኩት ምንጭ የተቀዳ መሆኑን በተጨባጭ ማስረጃ ስለማሳይ በትዕግስት ተከተሉኝ፡፡
    - መጽሐፍ ለመጻፍ የሚያበቃ ብስለትና አቅም ሳይኖረው ለገንዘብ ብሎ ያልተጣራ ሥራ ወደ ማተሚያ ቤት መውሰዱ ሌላው ምክንያት ነው፡፡ በተወሰኑ አጋጣሚዎች የሚጽፋቸውን ጽሑፎች ስላነበብኩኝ ልጁ ንግግር ላይ የተሻለ ቢሆንም ጽሑፍ ላይ ግን ደካማ በመሆኑ መጽሐፍ ለመጻፍ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን ሳውቅ ጥድፊያው ትክክል አለመሆኑን በተለያዩ መንገዶች ገልጬለት ነበር፡፡ እርሱ ግን ምክሩን በበጎ መንገድ ከማየት ይልቅ ከፍርሃት የመነጨ አድርጎ በአደባባይ ሲናገር ነበር፡፡ ምክር መስማት ያልፈለገውን ሰው ደግሞ በሚገባው ቋንቋ ማናገር ተገቢ ይመስለኛል፡፡
    - መጽሐፉን ያሳተመው በአረብ አገራት ከሚኖሩት እህቶቻችን ባሰባሰበው ገንዘብ ቢሆንም የልፋታቸውን ዋጋ የሚመጥን ሥራ አልሠራም፡፡ የችኮላው ብዛት በሽፋን ገጹ ላይ የሚገኘው የአረብኛ ጽሑፍ ስህተት እያለበት አሳትሞታል፡፡ በውስጡም ብዙ የፊደል ግድፈቶ አሉበት፡፡ ባጠቃላይ ኮምፒዩተር ላይ የሚለማመድ ተለማማጅ የጻፈው እንጂ ለመጽሐፍ ታስቦ የተጻፈ አይመስልም፡፡ መጽሐፉ ገበያ ላይ ከተበተነ በኋላ መጽሐፍት ሻጮች ስህተቱን በማስተዋላቸው ምክንያት ለመሸጥ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው እንደገና ተሰብስቦ ወደ ማተሚያ ቤት እንዲመለስ ሲባልም ነበር፡፡ ገንዘብ ለማግበስበስ ባይጣደፍ ኖሮ ይህ ሁሉ ኪሳራ አይኖርም ነበር፡፡ ማዘን ካለብኝ የማዝነው በአረብ አገራት እየተሠቃዩ ፈጣሪያቸውን ያገለገሉ መስሏቸው የላባቸውን ውጤት ለየሕያ ለላኩለት እህቶች እንጂ ለየሕያ አይደለም፡፡ የሕያ ተማሪዬ ቢሆንና አሳይመንቱን በዚህ መንገድ ጽፎ ቢያቀርብልኝ ይዘቱ ትክክል ቢሆን እንኳ በግድፈቶቹ ምክንያት ብቻ F እሰጠው ነበር፡፡

2. በኔ ማንነት ላይ ትኩረት ሳያደርግ መልስ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ቢናገርም ለመጀመርያዎቹ 15 ደቂቃዎች ግን ከሞላ ጎደል ያወራው ስለ እኔና ስለ ሌሎች ክርስቲያን ዐቃቤ እምነታውያን መሆኑ አስቂኝ ነው፡፡ ስለ እኔ ማውራት እንደማይፈልግ ከገለጸ ከ2ኛው ደቂቃ  በኋላ እንኳ እስከ 15ኛው ደቂቃ ድረስ ደጋግሞ እያነሳ አውርቷል፤ "በመልሱ" መሃል መሃልም በማንነቴ ላይ ያነጣጠሩ ቃላትን ሲወረውር ነበር፡፡ በሳል መስሎ ለመታየት ቢሞክርም እንጭጭነቱን መደበቅ አልቻለም፡፡
3. ክርስቲያን ዐቃቤ እምነታውያንን በማጣጣል የተናገራቸው ብዙ ነገሮች ከማሕበራዊ ሚድያ የዘለለ መረጃ እንደሌለው ያሳብቃል፡፡ ከአገራችን አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ እስልምና የሚያስተምሩና ከታላላቅ ሊቃውንት ጋር ትከሻ የሚለካኩ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ሊቃውንት አሉ፡፡ ሙስሊም ዳዒዎች ከአረብኛ አልፈው ግሪክና እብራይስጥን እንደሚችሉና ክርስቲያኖች ግን የአረብኛ ቃላትን እንኳ ከእንግሊዘኛ በመተርጎም በተሳሳተ አነባበብ እንደሚጽፉ የተናገራትን ነገር ስሰማ ከልቤ ስቄያለሁ፡፡ ምናልባት በእሱ ቤት የግሪክና የእብራይስጥ ሊቃውንት የሚላቸው *"ምኖጌኔስ ማለት የተፈጠረ ማለት ነው ምክንያቱም ዘፍጥረት የሚለው ቃል በግሪክ ጌኔሲስ ከሚለው የመጣ ነው"* ብሎ የሚያስተምረውን አንድ የፌስ ቡክ አርበኛ ወዳጁና *"ሆንትዮስ፣ ቶንትዮስ"* የሚሉ በግሪክ ቋንቋ የማይታወቁ ቃላትን የፈጠረውን ሰልማን ኮከብ የተሰኘውን ጓደኛውን ይሆናል፡፡ የነዚህን ሰዎች የግሪክ ዕውቀት ለማየት **እዚህ ጋ** ይንኩ፡፡ እነዚህ ወገኖች እንኳንስ ግሪክና እብራይስጥ ይቅርና አረብኛ እንኳ በወጉ እንደማያውቁ እየተዋወቅን ግሪክና እብራይስጥ ላይ መንጠራራታቸው የሚገርም ነው፡፡
4. ክርስቲያን ዐቃቤ እምነታውያንን እስላማዊ ቃላትን ከእንግሊዘኛ በቀጥታ በመተርጎም የሚከሰው ይህ ሰው የገዛ ወገኖቹ ስለ ክርስትና በሚጽፉበት ጊዜ ተመሳሳይ ስህተቶችን መፈጸማቸውን እንዴት ይመለከት ይሆን? ለምሳሌ ያህል ዑመር አርሲ የተባለ ጸሐፊ "ታላቅ ምክር…" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ "የአስቆሮቱ ይሁዳ" እንደማለት ከእንግሊዘኛ በቀጥታ በመተርጎም "ጁዳስ እስካርዮት" ብሎ ጽፏል (ገፅ 45)፡፡ የሕያ በዚህ ንግግሩ ውስጥ ያሞገሰው ሐሰን ታጁ ደግሞ "የሐመረ ተወሕዶን ቅጥፈት…" በሚለው መጽሐፉ ውስጥ ‹ኖስቲክ› የሚለውን ‹ግኖስቲክ› ብሎ ጽፏል (ገፅ 103)፡፡ (Gnostic የመጀመርያዋ ፊደል ድምፅ አልባ ናት፡፡) ይባስ ብሎ ‹ኮዴክስ ሲናይቲከስ› የሚለውን ‹የሲያትል ጽሑፍ› ብሎታል (ገፅ 43)፡፡ የቅርብ ወዳጁ ሰልማን ኮከብም "ንቁ" በሚለው የኩረጃ መጽሐፍ ውስጥ ጠርጡሊያኖስን በቀጥታ ከእንግሊዘኛ በመተርጎም "ቴርቱሊያን" ብሎታል (ገፅ 61)፡፡ መርቂያን የሚለውን "ማርኪዮን"፣ ኖስቲክን "ጊኖስቲክ"፣ ሰባልዮሳውያንን "ሴባሉሳውያን"፣ ወዘተ. ብሎ ጽፏል (ገፅ 64፣ 65)፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ክርስቲያኖች እስላማዊ ስሞችን ከእንግሊዘኛ በቀጥታ መተርጎማቸውን እንደ ዕውቀት ጉድለት በመቆጠር ብዙ ያወራው የሕያ እነዚህ ወገኖቹ ተመሳሳይ ነገር መፈፀማቸውን ሲያስተውል ክርስቲያኖችን እንደ ዘለፋቸው ሁሉ ይዘልፋቸዋል ወይንስ "አስቶጉፉሩላህ!" ብሎ ያልፋቸዋል?
5. የሕያ በዚህ ኦዲዮ ውስጥ ከዚህ ቀደም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ "ግጭቶች" ለጻፈው መጽሐፍ መልስ መስጠት የቻለ ክርስቲያን አለመኖሩን አፅንዖት ሰጥቶ አውርቷል፡፡ ከአባባሉ እንደተረዳሁት ለተከታዮቹ "ለዚህችኛዋ መጽሐፍ መልስ ቢሰጡም ያችኛዋን አልቻሏትምና አይዟችሁ" የሚል ዐይነት መልእክት ለማስተላለፍ የፈለገ

ይመስላል፡፡ የሕያ በአደባባይ ሱሪው ወልቆ እየተሳቀበት ሳለ “ሱሪዬ ቢወልቅ ምንም አይደለም፡፡ ኮፍያዬን አያችሁ? በጣም ታምራለች እኮ! የነቢዩ ሱና ናት! ከታች ካልሲዬን ተመልከቱ የቱርክ ስሪት ናት!” እያለ ሐፍረቱን ለመሸፈን እንደሚሞክር ሰው ነው፡፡ ያችኛዋ መጽሐፉ ምንም ያህል “ጠንካራና ኦሪጅናል” ብትሆን ይህቺኛዋ ግን ደካማና ኩርጅ መሆኗ ስለተጋለጠ የየሕያ “ያቺን ከሒሳብ ውስጥ አስገቡልኝ” ልምምጥ ዋጋ የለውም፡፡

6. የሕያ መጽሐፉን ከጠቆምኩት ድረገፅ ላይ መኮረጁን ቢክድም ጽሑፉን ከዚህ ቀደም እንደሚያውቀው አምኗል፡፡ ጽሑፉን ማወቁን አለመካዱም አንድ ነገር ሆኖ ያነሳቸው ነጥቦች ከዚህ ቀደም በሌሎች ሙስሊሞች የተነገሩ መሆናቸውን ዋቢ በማድረግ ከዚህ ጽሑፍ አልኮረጅኩም ብሏል፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን የሐሳብ መመሳሰል ሳይሆን ቃል በቃል መስመር በመስመር ተቀድቶ የተተረጎመ መሆኑ ነው፡፡ “የሌባ ዐይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ” እንደሚለው ብሒል የሕያ “አልኮረጅኩም፣ ዐይኔን ግንባር ያድርገው” ብሎናል፡፡ እኔ ደግሞ በበኩሌ የሕያ የጻፈውንና በእንግሊዘኛ የተጻፈውን የተወሰኑትን ለናሙናነት ጎን ለጎን አድርጌ ፍርዱን ለአንባቢያን እሰጣለሁ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. <u>ስቅለት ለምን?</u><br>አይሁዳውያን እየሱስን ሊሰቅሉት የፈለጉበት ዋነኛ አላማ እርሱ የሚወደድ የአምላክ ልጅ እንዳልሆነና የአምላክ እርግማን በርሱ ላይ እንደነበር በወቅቱ ለነበረው ህዝብ ለማሳየት ነበር። አይሁዳውያን ከብዛት አንፃር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ እንደመሆናቸው መጠን እየሱስን በቀላሉ ለመግደል የሚያዳግታቸው ምንም ነገር አልነበረም። አላማቸው እንዲሁ ዝምብሎ እሱን መግደል ቢሆን ኖሮ ልክ ሰላሳ ዲናር ከፍለው እንዳገኙት ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ከፍለው ማስገደል ይችሉ ነበር። ነገር ግን ዋነኛ አላማቸው በአደባባይ አዋርደ በፍርድ በማስገደል ለሌላው ህዝብ ከአምላክ ያልተላከ ሀሠተኛ መሲህ እንደሆነ ማሳየት ነበር። በርግጥም ከአምላክ ዘንድ ከሆነ ያለምንም ጥርጥር አምላክ ያድነዋል ካልሆነ ግን ልክ እንደማንኛውም ወንጀለኛ ነው የሚለውን ህዝቡ ይረዳ ዘንድ ይፈልጉ ነበር። ይህ በአይሁዶች ዘንድ የነበረው አመለካከት ነበር። በዚህ ረገድ ላስተዋለ ሰው እየሱስ መሰቀሉ የነሱን አላማ ያሳካዋል እንጅ የተለየ ትርጉምን አይሰጠንም። | **1. Why crucifixion?**<br><br>Jews wanted him to be killed through crucifixion, so they can prove that Jesus is not a beloved of God, rather the curse of God is on him. Jews could have killed him easily as they were in hundreds of thousands in number and very strong. If killing should have been their desire, they could have done it easily. Just like they paid thirty pieces of silver to one of his disciples, if they would have paid him more, he might have done this service too. But they wanted him to be crucified so they can prove that he is not from God, rather he is an imposter and a fabricator. If he was from God, then God will definitely save him. May be that was the reason that Jesus was so reluctant to suffer on the cross. |

## 2. ይሰቀል ዘንድ ማን ፈለገ?

እየሱስ ይሰቀል ዘንድ ይፈልጉ የነበሩት እነማን ናቸው? የሚለውን አስመልክቶም መፅሀፍ ቅዱስ ወጥ የሆነ ትምህርት የለውም። በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ሰዎችን በመጥቀስ በዚህ ዘርፍ ሊኖረው የሚገባውን ግልጽነት ነፍገውታል። ሉቃስ ለዚህ ተግባር የካህናት አለቆችንና መኳንንቶችን ተጠያቂ ያደርጋል።

*"፤ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው።" (የሉቃስ ወንጌል 24:20)*

በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ይህንን ቅጣት ይፈልጉ የነበሩት ጥቂት ሰዎች ሳይሆኑ ህዝቡ ሁሉ እንደነበር ይነግረናል።

*ጲላጦስ፡- ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም፡- ይሰቀል አሉ። ገዢውም፡- ምን ነው?ያደረገው ክፉት ምንድር ነው?አለ፤ እነርሱ ግን፡- ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ። ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ፡- እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ። ሕዝቡም ሁሉ መልሰው፡- ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። (የማቴዎስ ወንጌል 27:22-25 )*

**ታዲያ እየሱስ ይሰቀል ዘንድ የፈለጉት እነማን ናቸው? ጥቂቱ ማህበረሰብ ወይንስ መላው ህዝብ? ይህም በስቅለት ታሪክ ውስጥ ካሉ ያልጠሩ ብዥታዎች መካከል አንዱ ነው።**

## 3. ስቅለቱን የፈለጉት አይሁዳውያን ነበሩ

የእየሱስ ስቅለት በዋነኝነት ትርጉም የሚሰጠውና ጠቃሚ የሆነው ለክርስቲያኖች ነው። እንደ ክርስቲያኖች አመለካከት እየሱስ ለእነሱ ሀጥያት ብሎ በመስቀል ላይ በመሞት እዳቸውን ከፍሎላቸዋል። ነገር ግን የስቅለትን ዳራ ስንመለከተው ግን የስቅለቱ ታሪክ ወደዚህ የእምነት ሒደት አይመራንም። በአንድ ወቅት በአይሁዳውያንና በሱ መካከል በነበረ አለመግባባት አይሁዳውያን እንዲሞት በመፈለጋቸው ምክንያት በገዥው ፊት አቅርበው እንዲፈረድበት አድርገዋል። በቃ ታሪኩ አበቃ።

*ጲላጦስም፡- እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ፡- ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፡- እኔስ እንዴት በደል ስንኳ አላገኝሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት አላቸው። አይሁድም መለሰው፡- እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጓአልና አሉት።*

*(የዮሐንስ ወንጌል 19:6-7)*

## 2. Who wanted him to be crucified?

Two of Jesus' disciples commented (in Luke 24:20) as follows:

> And how the chief priests and our rulers delivered him to be condemned to death, and have crucified him. (Luke 24:20)
>
> They all say unto him, Let him be crucified. And the Governor said what evil hath he done? But they cried out the more, saying Let him be crucified.... Then answered all the people, and said, His blood be on us, and on our children. (Matt 27: 22-25)

> When the chief priests therefore and officers saw him, they cried out, saying, Crucify him, crucify him. (John 19:6)
>
> The Jews answered him (Pilate), We have a law, and by our law he ought to die, because he made himself the Son of God. (John 19:7)

<table>
<tr>
<td>
4. <u>ክስተቱ አንድ ሲሆን ምልከታው ግን ይለያያል</u><br>
➢ ሮማውያን ስቅለቱን ለሀገር ክህደት ወንጀል የተላለፈ ቅጣት እንደሆነ ያምናሉ<br>
➢ አይሁዳውያን ደግሞ ለሀይማኖት <u>ክህደት የተፈጸመ</u> ቅጣት አድርገው ይወስዱታል።<br>
➢ ኢየሱስ ደግሞ ከደቀመዛሙርቱ መካከል አንዱ አሳልፎ በመስጠቱ ሳቢያ የተፈጸመ ግድያ እንደሆነ ያምናል።<br>
➢ ክርስቲያኖች ደግሞ ለሀጥያታቸው ማስተሰሪያ የተደረገ መስዋዕትነት እንደሆነ ያምናሉ።<br>
ታዲያ የትኛው ነው ትክክል?
</td>
<td>
4. <u>One incident and many aspects</u>?<br>
1. Romans took it as <u>punishment of sedition</u>.<br>
2. The Jews made it as a <u>punishment of blasphemy</u>.<br>
3. Jesus considers it <u>a killing</u>, when one of his disciples betrayed him.<br>
4. Christians think <u>a sacrifice</u> presented for our salvation.
</td>
</tr>
</table>

በቦልድ የጻፋቸውን ነጥቦች ልብ በሉ፡፡ **ለሀገር ክህደት፣ ለሀይማኖት ክህደት የተፈጸመ ቅጣት፣ ግድያ፣ ለሀጥያታቸው ማስተሰሪያ፣** የሚሉትን ቃላት የሕያ አጥቁሮ የጻፈ ሲሆን ኦሪጅናል ለእንግሊዘኛ ጽሑፉ ላይ እነዚሁ ቃላት ጠቁረዋል፡፡ ይህ በቀጥታ ከዚህ ጽሑፍ ላይ ለመውሰዱ በቂ ማሳያ አይደለምን? ሀቱ!

| | |
|---|---|
| 5. <u>የኢየሱስ መደበቅ</u><br><br>ኢየሱስ ከአይሁዳውያን ቅጣት ለማምለጥ በማሰብ በተለያዩ ጊዜያት ይደበቃቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ባለመቻላቸው ነበር ይሁዳን መረጃ እንዲሰጣቸው መደለያ የከፈሉት።<br><br>*" ወደ ቤቱም ሰደደውና:- ወደ መንደሩ አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር አለው።"*<br><br>*(የማርቆስ ወንጌል 8:26)*<br><br>*"ስለ እርሱም ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው።"*<br><br>*(የማርቆስ ወንጌል 8:30)*<br><br>ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋነኛ አለማ ለሰው ልጆች ሀጥያት መሠቀል ከነበረ ለምን ይደበቃል? መሸሸስ ለምን አስፈለገው? | 5. **<u>Why Jesus was hiding?</u>**<br><br>That's why the Jews paid thirty pieces of silver to Judas giving them the necessary information about Jesus.<br><br>> ...Neither go into town, nor tell it to any in the town. (Mark 8: 26)<br><br>> And he charged them that they should tell no man of him. ((Mark 8: 30) |

6. <u>ከስቅለት ይድን ዘንድ የእየሱስ ጸሎት</u>

እንደ ክርስቲያኖች እምነት መሰረት ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋነኛ ዓላማ ለሰው ልጆች ተሰቅሎ ለሀጥያታችን ቤዛ ሊሆን ነው።

*" አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።"*

*(የዮሐንስ ወንጌል 12:27)*

*"ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፦ አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።"*

*(የማቴዎስ ወንጌል 26:39)*

*«ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም፦ አባት ሆይ፥ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።» (የሉቃስ ወንጌል 22:41-42)*

**እንደ ክርስቲያኖች አመለካከት መሰረት ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ተሰቅሎ ለሀጥያታችን ቤዛ ይሆን ዘንድ ነው። ይህ ከሆነ አላማው ታዲያ ይህ ሁሉ ልመናና ጸሎት ምንን በማስመልከት ነው? ሊሞት እንደመጣ አያውቅም? ወይንስ በመጨረሻ ሀሳቡን ቀይሯል?**

6. <u>**Jesus' prayers and supplications**</u> to be saved from crucifixion:

> Sit ye here, while I go and pray yonder. (John 26: 36)
>
> And he went a little further, and fell on his face, and prayed, saying, O my father, if it be possible, let this cup pass from me. (John 26: 39)
>
> .... He went away again, and prayed the second time and prayed, saying ......and prayed the third time, saying the same words. (John 26:42-44)

ኦሪጅናል ጽሑፉ ላይ የጥቅሶቹ ምዕራፎችና ቁጥሮች ስህተት በመሆናቸው የሕያ አስተካክሏቸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| 7. <u>አምላክ ሁሌም ልመናውን ይሰማው ነበር።</u><br><br>ዩሀንስ በወንጌሉ እንደሚገልፀው የእየሱስ ፀሎት ሁሌም ተቀባይነት ያለው ነበር። ይህንን አስመልክቶ እራሱ እየሱስ እንዲህ ይላል፡-<br><br>*ድንጋዩንም አነሡት፡- ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ፡- አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ..(የዮሐንስ ወንጌል 11:41- 42)*<br><br>ታዲያ በዚህ አንቀፅ እንደተቀመጠው እየሱስ ፀሎቱ የሚሰማለት ከሆነ እንዳይሰቀል ያደረገው ፀሎት ምን ውሀ በላው? በሌላ ቦታ ደግሞ ጭራሽ ፀሎቱ ተሰምቶ እንደነበር ጳውሎስ ይናገራል።<br><br>*"እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤"*<br><br>*(ወደ ዕብራውያን 5:7)*<br><br>ከሞት ወደ ሚያድነው አካል ፀሎት አድርጎ ፀሎቱ ከተሰማለት እየሱስ አልሞተም ነበር ማለት ነው። | 7. <u>God always hears his prayers</u> and <u>his prayers were heard</u><br><br>> And Jesus lifted up his eyes, and said, Father, I think thee that thou hast heard me. And I knew that thou hearest me always. (John 11:41-42)<br><br>> Who in the days of his flesh, when he had offered up prayers and supplications with strong crying and tears unto him that was able to save him from death, and was heard in that he feared. (Hebrews 5:7) |

**8. <u>እየሱስን ሊያበረታ መልዐክ ወርዶ ነበር?</u>**

በወንጌል እንደተገለጸው በመጨረሻዎቹ የኢየሱስ ጊዜያት ያበረታው ዘንድ መልዐክ ወርዶለት ነበር።

*ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር። ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአከ ታየው። (የሉቃስ ወንጌል 22፡42-43 )*

የዚህ መልዐክ ብርታት ማሳያው ምንድን ነበር? ከላይ እንደተመለከትነው እንዳይሞት ፀለየ ከዚያም መልዐክ ወርዶ አበረታው፤ በሌላ አነጋገር እየሱስ ይፀልየው ለነበረው ተማፅኖ እምላክ ምላሹን በመልዐኩ በኩል ልኳል ማለት ነው። የሱ ተማፅኖ ምላሽ ካገኘ ደግሞ በአጭር ቃል "አልተሰቀለም ነበር" ማለት ነው።

**8. <u>An Angel was sent to strengthen Jesus?</u>**

> And there appeared an angel unto him from heaven, strengthening him. And being in an agony he prayed more earnestly: and his sweat was as it were great drops of blood falling down to the ground. (Luke 22: 43-44)

**9. <u>ጲላጦስ ፍርዱን አዘግይቶት ነበር</u>**

ጲላጦስ ሆን ብሎ የስቅለቱ ጊዜ እንዲራዘምና ውሳኔ እንዳይሰጠው አዘግይቶት ነበር። ይህም ቀኑ ሰንበት በመሆኑ ምክንያት መስቀል ላይ

ለጥቂት ጊዜያት እንደሚቆይ ተረድቶ ነበር። የ33 አመት ወጣት የነበረው እየሱስ በመስቀል ላይ የቆየው ከ3-6 ለሚሆኑ ሰአታት ብቻ ነበር። አንድ ሰው በነዚህ አነስተኛ ጊዜያት ውስጥ የመሞት እድሉ በጣም የተመናመነ ነው። ስቅለቱ አካሉን ይጎዳው ይሆናል እንጅ መሞት የሚያደርስ አልነበረም። በሮማውያን የአገዛዝ ጊዜ በስቅለት ይሞቱ የነበሩ ሰዎች ቢያንስ ሁለት ቀን ይፈጅባቸው ነበር።

**9. <u>Pilate delays in judgment</u>**

Pilate intentionally delayed in giving his verdict and did not deliver his judgment until and unless he was sure that due to the Sabbath, Jesus would be on the cross for only a few hours. Jesus a thirty-three years young person was on the cross for only few (3-6) hours.

ቃል በቃል ትርጉም፡፡

10. <u>ጲላጦስ የዋለው ውለታ</u>

ጲላጦስ ኢየሱስን ነፃ ሰው ነው ብሎ በማሰብ ትልቅ ውለታ ሲውልለት ነበር። በሚስቱ ህልም ምክንያትም ያድነው ዘንድ ይጥር ነበር። ለዛም ነበር አይሁዶች ባይስማሙም ያለውን ልዩ መብት ሊጠቀም የሞከረው

*«እንግዲህ እነርሱ ተሰብስበው ሳሉ ጲላጦስ፡- በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፡- ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት። የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ። ገዢውም መልሶ፡- ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ እነርሱም፡- በርባንን አሉ። ጲላጦስ፡- ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም፡- ይሰቀል አሉ።ገዢውም፡- ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አለ፤ እነርሱ ግን፡- ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ። ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ፡- እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ።» ማቴዎስ 27፡17-24*

ይህንን የጲላጦስ ተግባር ለተመለከተ ሰው ኢየሱስን በግዴለሽነት እስከ መጨረሻው እንዳሰቀለው ለማሰብም ለመገመትም ይከብዳል።

10. **<u>Pilate's complete favor to Jesus</u>**

Pilate was in complete favor of Jesus, considering him innocent, and for his wife's dream, was trying to save his life. That's why Pilate wanted to use his special right to free one person, but the Jews did not let him do it.

> Pilate said unto them, whom will ye that I release unto you? Barabbas or Jesus.... But the chief Priests and the elders persuaded the multitude that they should ask Barabbas, and destroy Jesus. The Governor answered and said unto them, whether of the twain will ye that I release unto you? They said Barabbas. Matt 27: 17-21)

| | |
|---|---|
| 11. <u>የጲላጦስ ሚስት ህልም</u><br><br>*"እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፡- ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት።" (የማቴዎስ ወንጌል 27:19)*<br><br>ይህ ህልም እንዴት ከኢየሱስ ተልዕኮ በተቃራኒ ሊሆን ቻለ? እንደ ክርስትያኖች እምነት መሠረት የእየሱስ ዋነኛ ተልዕኮ ወደዚህ ምድር መጥቶ ለሰው ልጅ ሀጥያት መሞት ነው። የጲላጦስ ሚስት ህልም ግን ከዚህ ተልዕኮው በተቃራኒ ነበር። ይህ ህልምም በመፅሀፍ ቅዱስ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት ተዘግቦ እናገኘዋለን፤ በአንዳንድ የክርስትና የታሪክ መፅሀፍት ውስጥም ሴትየዋን እንደመልካም ሰው ተስላ እናገኛለን። ህልሙ ተራ ከነበረና ለታሪኩ ጠቃሚ ካልነበር በመጽሀፍ ቅዱስ የመዘገቡ ቁምነገር ምንድን ነው? | 11. **<u>Pilate's wife sees a dream to save Jesus</u>**<br><br>When he sat down on the judgment seat, his wife sent unto him saying, Have thou nothing to do with that just man: for I have suffered many things this day in a dream because of him." (Matt 27:19)<br><br>Why was this dream was against the purpose of the advent of Jesus, to give his life on the cross? Her dream should have been that crucify him immediately. Let him finish his work. But her dream was against it. Although her dream was so special that it was mentioned in the Bible. |

| | |
|---|---|
| 12. <u>የእግዚአብሄር ቁጣ</u><br>የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የፀሀይ ግርዶሽና መብረቅ የአምላክ ቁጣ ማሳያዎች ናቸው። ይህንን አስመልክቶ ለአብነት የዳዊትን ንግግር መጥቀስ እንችላለን<br>*" ምድርም ተንቀጠቀጠች ተናወጠችም፥ የተራሮችም መሠረቶች ተነቃነቁ፥ እግዚአብሔርም ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ።"*<br>*(መዝሙረ ዳዊት 18:7)*<br>እነዚህተግባራት ታዲያ በእየሱስ ስቅለት ወቅት ታይተው ነበር። ከዚህ የምንረዳው ነገር ተግባሩ አይደለም ለሰው ልጅ መዳኛ የተፈጸመ ተግባር ሊሆን ይቅርና አሳዛኝና አምላከን ያስቆጣ ጭምር እንደነበር ነው። | 13. <u>Earthquake, eclipse & a storm – A sign of God's disliking & anger</u><br><br>An earthquake, eclipse of Sun and a Storm, all three occurred just after the crucifixion is a clear sign of God's anger.<br><br>> Now from sixth hour there was darkness over all the land unto the ninth hour. (Matt 27:45)<br><br>> ...the earth did quake, and the rocks rent. (Matt 27: 51) |

በእንግሊዘኛው ቁጥር 12 ላይ የሚገኘውን ከጥያቄ ቁጥር 10 ጋር አንድ ላይ ስለቀላቀለ አሸጋሽጓል፡፡

13. <u>የጲላጦስ መገረም</u>

*" ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቶአልን? ብሎ ጠየቀው፤"*

*(የማርቆስ ወንጌል 15:44)*

ጲላጦስ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ሲነገረው በዚህ ፍጥነት እንዴት ሞተ? ሲል ተደንቋል። እንግዲህ ሁላችንም እንደምናውቀው ጲላጦስ በዚህ ዘርፍ እጅግ ልምድ ያለው ሰው ነበር፤ የሮማ ገዥዎች ሰዎችን በስቅላት መቅጣት የተካኑበት ተግባር ነው። ይህ ግርምቱ የመጣውም ከዚህ የተነሳ ነበር። አንድ የ33 አመት ያላገባ ወጣት በጥቂት ሰአታት ውስጥ እንደማይሞት ያቀዋል።

14. <u>**Pilate marveled**</u>

> And Pilate marveled if he were already dead. (Mark 15: 44)

When Pilate was informed about the death of Jesus on the cross, he marveled at hearing it. We know that Pilate was the most experienced person in this field; who may have experienced hundreds of crucifixions in his time. That is why; he knew very it well that a 33 years, unmarried young person shouldn't die in few hours, while the other two thieves (elder than him) were still alive after the crucifixion.

14. <u>አብረውት የተሰቀሉት ወንበዴዎች</u>

እየሱስ ሲሰቀል አብረው ተሰቅለው የነበሩ ሁለቱ ወንበዴዎች አልሞቱም ነበር። በዛም ምክንያት ወታደሮቹ እግሮቻቸውን ሰብረዋቸዋል።

*“ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤”* (የዮሐንስ ወንጌል 19:32)

**አብረውት የተሰቀሉት ግለሰቦች ሳይሞቱ ኢየሱስ እንዴት ሊሞት ይችላል? የተለየ ፍርድ እሱ ጋር ቢኖር ምናልባት ልንጠረጥር እንችል ይሆናል። ነገር ግን ሁሉም አብረውት የተሰቀሉ ተመሳሳይ ቅጣት የሚፈጸምባቸው ግለሰቦች ናቸው።**

15. **The other two (thieves) next to Jesus were still alive** so **they broke their legs**

> Then came the soldiers, and brake the legs of the first, and of the other which was crucified with him. (John 19: 32)

15. <u>ደምና ውሃ</u>

ወታደሩ የእየሱስን ጎን ሲወጋው ደምና ውሃ ወጥቶት ነበር፤ ይህ ደግሞ በህይወት እንደነበር የሚያረጋግጥልን ክስተት ነው። አንድ ሰው

ሲሞት ደሙ ወዲያውኑ ይረጋል። ደሙ ግፊት ኖሮት መፍሰስ ቻ
ማለት ግን የልብ ምቱ ነበረ ማለት ነው።

*"ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደም ውኃ ወጣ።" (የዮሐንስ ወንጌል 19: 34)*

**በጸሀፊው ዘገባ ውስጥ ደም መውጣቱን የሚገልፀው ክፍል ለም ትኩረት ተሰጥቶት ሊዘገብ ቻለ? የሚለው ጥያቄ እዚህ ጋር መሠረታ ይሆናል።**

" ስለ እነዚህም የመሰከረ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀ መዝሙር ነው ምስክሩም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።"

(የዮሐንስ ወንጌል 21: 24)

**ጸሀፊው ከምንም በላይ በምስክርነቱ ተዓማኒነት ዙሪያ ትኩረ ሲያደርግ እናስተውላለን። ይህም ማለት የደም መውጣቱን ታሪክ መሠል መግለጽ ያሉበትን ምስክርነቶች መሸሸግ አልፈለገም ማለ ነው።**

16. **<u>Blood and Water – a great sign of Jesus' life</u>**

When a soldier pierced a spear in Jesus' side, blood and wate gushed out from his body, with full pressure, is a sign and a witness that Jesus' heart was still pumping and he was alive

> But one of the soldiers with a spear pierced his side, and forthwith came there out blood and water. (John

Why coming of blood and water is so important that the narrator of the incident specially describes:

> And he that saw it bare record, and his record is true: and he knoweth that he saith true, that ye might believe. (John 19:35)

<table>
<tr>
<td>

16. <u>ለሞቱ ማረጋገጫ</u>

ወታደሮቹ የእየሱስን መሞትና አለመሞት ለማረጋገጥ ለምን ጎኑን መውጋት አስፈለጋቸው? ሌላ አይነት የማወቂያ መንገድ አልነበረምን?

መሞትና አለመሞቱን ለማረጋገጥ ጎኑን መውጋታቸው በጭራሽ ስሜት የሚሰጥ ነገር አይደለም። ምናልባት ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ ሲጠቀሙ ካልነበረና ብቸኛ ማረጋገጫቸው ይህ ከነበረ ሊያስኬድ ይችላል። ለምንስ ያንን ተግባር ፈጸሙ? መሞት አለመሞቱን ለማወቅ ከተባለ ሌሎች አብረውት የተሰቀሉትንም በተመሳሳይ ጎናቸውን መውጋት ነበረባቸው። ይህ በታሪኩ ውስጥ የተጨመረ የተዛነፈ ትርክት እንደሆነ በቂ ማሳያ ነው።

</td>
<td>

17. <u>Why the soldiers checked Jesus alive or dead, piercing him a spears. What was the criteria, then to recognize?</u>

The concept that one of the soldiers pierced Jesus a spear to check him, either he is alive or not, does not make any sense until and unless there was really a way of checking this way. Piercing Jesus a spear or some other way? What was that? How did they do it? Because one of the soldiers pierced a spear in Jesus' body. Not to check his life or death. Otherwise they should have done the same with other two also.

</td>
</tr>
</table>

<table>
<tr>
<td>

17. <u>የእየሱስ ጭኖች አልተሰበሩም ነበር።</u>

*"ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤" (ዮሐ 19: 33)*

ከጥግ የነበሩት ሁለቱ ሳይሞቱ ኢየሱስ መሞቱ የሚገርም ከመሆኑ በተጨማሪ የጭኑ አለመሰበር ደግሞ ይበልጥ ጥያቄ ያጭራል። ጭኑ ያልተሰበረው ስለሞተ ከሆነ አንደኛው ወታደር ጎኑን መውጋት ለምን አስፈለገው? ሙቷል ብለው ጭኑን ካልሰበሩት መልሰው የሚወጉበትስ ምክንያት ምንድን ነው?

</td>
<td>

18. <u>**Jesus legs were not broken**</u>

> But when they came to Jesus, and saw that he was dead already, they broke not his legs: (John 19:33)

</td>
</tr>
</table>

**18. <u>እየሱስ በመቃብር ውስጥ አልተቀበረም ነበር።</u>**

እንደሚታወቀው የአይሁዳውያኑ የሺህ አመታት ልማድ አንድ ሰው በሚሞትበት ሰዓት መሬት ቆፍሮ መቅበር ነው። እየሱስ ግን እንደዛ አልተቀበረም። የወሰዱት አየር ያለበትና ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ ነበር። ይህ ደግሞ እየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ ያውቁ እንደነበር በቂ ማሳያ ነው። አፈር ቆፍረው ቢቀብሩት እንደሚሞት ያቃሉ ስለዚህ የተሻለው አማራጭ ሰፋ ያለ ቤት ውስጥ በማስገባት እስትንፋሱን ማቆየት ነው።

**19. <u>Jesus was not buried in the grave</u>**

The Jewish custom for the last thousands of years was to bury the deceased in the ground. Because the disciples knew the predictions, which were made earlier by Jesus Christ, they kept Jesus' body in a sepulcher. If they had buried him in a grave, he would have died. But his disciples placed him in a roomy "Sepulcher?" Rather then burying him in the ground according to the Jewish custom and traditions.

**19. <u>መሞቱን ማን እርግጠኛ መሆን ይችላል?</u>**

እንደ መጽሀፍ ቅዱስ ገለጻ እየሱስ በሞተበት ወቅት ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥና የመብረቅ ብልጭታ ነበር። በተጨማሪም የጸሀይ ግርዶሽ ሳይቀር ተከስቶ ነበር። በዚህ ሰዓት ሊፈጠር የሚችለውና መደናበርና ሩጫ ማንም የሚገምተው ነው። ይህ መብረቅና የመሬት መንቀጥቀጥ ያደናበረው ህዝብ እየሱስ ለመሞቱ እንደማስረጃ የሚቀርብ አይደለም። እርሱ በተሰቀለበት ሰዓት እነርሱ ነፍሳቸውን ለማዳን ሲሸሹ ነበር። ታዲያ ማነው ከመነሻው እስከመጨረሻው በቦታው በሞሆን የአይን ምስክር ሊሆን የሚችለው? የለም

**20. <u>Neither Jews nor Christians are sure about Jesus' death on the cross</u>**

There was a very strong earthquake, a storm and an eclipse of sun just after the crucifixion of Jesus, that made all Jews and Romans run away from the sight. That is why; neither Jews nor the Christians are sure about the death of Jesus on the cross but a gesture.

**20. <u>ድንጋዩ በቦታው አልነበረም</u>**

ከሞት ለተነሳ አካል ይወጣ ዘንድ ድንጋይ አያግደውም። ድንጋይ እንዲፈቀ መውጣትም አይጠበቅበትም። ነገር ግን ያልሞተ የተለመደ ሰው አካል ከሆነ ግን ድንጋይ አንስቶ መውጣት ይኖርበታል። በዚህ መልኩ ካየነው እየሱስ እንዳልሞተ እንረዳለን። መግደላዊት ማርያም ልትነካው ባለች ጊዜም «አትንኪኝ»ብሎ ሲከለከላት እናስተውላለን።

*««ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ...»*

*የሀንስ 20:17*

**ጥያቄው ለምን አትንኪኝ አላት? ገና አላረግሁም ሲልስ በትክክል ምን ማለቱ ነበር? ገና አለመሞቱን (ነፍሱ ወደ አባቱ አለመሄዱን) እና አካሉ የቀድሞው ያልሞተው አካሉ እንደሆነ መግለጹ ነበር።**

**21. <u>The stone on the sepulcher was removed</u>**

(For a spirit, does not need to remove the stone)

Jesus forbade Mary Magdalene to touch him.

> Touch me not. (John 20:17)

Why?

**22.** Jesus said, " **<u>He has not ascended yet</u>**. What did he really mean?

> Jesus said unto her (Mary Magdalene), touch me not; for I am not yet ascended to my Father: but go to my brethren, and say unto them, I ascend unto my Father, and your Father; and to my God and your God. (John 20:17)

What are the real **<u>meanings of ascension</u>** here, when Jesus said to Mary "I am not yet ascended to my Father."

Certainly, it was understood and very clear without any doubt that Jesus had not ascended yet, while he was standing just in front of her. Then why Jesus said that he was not ascended yet?

21. <u>ምንም አልተደነቀችም</u>

ማርያም ኢየሱስን በህይወት ስታየው ምንም መደነቅ አላሳየችም ነበር። ለምን? ተሰቅሎ ሙቶ ነበር ብላ የምታስብ ከሆነ በህይወት ስትመለከው መደነቅ ነበረባት። ነገር ግን ይህንን አስመልከቶ ምንም የተነገረን ነገር የለም። እንዲሁ መደበኛ የቃላት ልውውጥ ማድረጋቸውን ብቻ ነው መጽሀፉ ላይ የምናገኘው። ይህ ደግሞ ለምን የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል።

23. **<u>Mary did not react, when she saw Jesus alive.</u>** Why?

22. <u>የኢየሱስ መብላት</u>

ደቀመዛሙርት ወደ ነበሩበት የላይኛው ክፍል ኢየሱስ ሂዶ በነበረበት ወቅት የተከሰተውን ክስተት ወንጌላት እንደሚከተለው ዘግበውት እናገኛለን።

«እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለላም ሰጡት፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ።» ሉቃስ 24:42-43

«ኢየሱስም፦ ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ፦ አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና። ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን።» ዮሀንስ 21:12-13

የሰው ልጅ አካሉ እንጅ መንፈስ ከሆነ ምግብና መጠጥ አያስፈልገውም። ኢየሱስ ደግሞ ሙቶ ተነስቷል። ሙቶ የተነሳ አካል በጭራሽ ምግብን ሊመገብ አይችልም። ታዲያ እየስ ሙቶ ከተነሳ እንዴት ምግብ ሊመገብ ቻለ?

25. **<u>Jesus ate food</u>**, in the presence of his disciples.

> … he said unto them, have ye here any meet? And they gave him a piece of a **<u>broiled fish</u>**, and an **<u>honeycomb</u>**. And he took it, and did eat before them. (Luke 24:41-42)
>
> Jesus saith unto them, come and dine. And none of the disciples durst ask him, Who are thou? Knowing that it was the Lord. Jesus then cometh, and taketh bread, and giveth them, and fish likewise. (John 21: 12-13)

A spirit does not need any food but our physical body, which becomes weak after a while, without having food. Why Jesus needed food, if he had gone back to his original body of God.

የተቀሩትንም ጥያቄዎች በዚህ መንገድ በማመሳከር እውነቱን ማየት ይቻላል፡፡ ራሳችሁ https://themuslimtimes.info/2012/04/14/65-reasons-to-believe-jesus-did-not-die-on-the-cross/ ድረገፅ ላይ ገብታች ተመልከቱ! በዚህ ገፅ ላይ የሌለ የሕያ ያቀረበው አንድም እደግመዋለሁ አንድም ጥያቄ የለም! ከሐሳብ መመሳል ባለፈ የቃል በቃል ትርጉም ነው፡፡ የሕያ ሆይ፤ እንግሊዘኛ የምታውቀው አንተ ብቻ ነህ ወይንስ ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ከኢንተርኔት ላይ ለዚያውም ከአንድ ገፅ ላይ አውርደህ መጽሐፍ ስትጽፍ እንዴት ትንሽ እንኳ ኅሊናህን አልጎረበጠህም? አሁን ከተጋለጥክ በኋላስ ስህተትህን አምነህ ይቅርታ እንደመጠየቅ ዐይንህን በጨው አጥበህ መዋሸትህ የጤና ነው? እውን እንዲህ እየቀጠፍክ እውነተኛና ጻድቅ የሆነውን ፈጣሪ እያገለገልኩ ነው ብለህ ታምናለህ? የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው አምላክ ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ እውነተኛና ሃያል ነው፡፡ ክብሩንና ግርማውን የሚያቃልል እንዳንተ ያለ ውሸታም ጠበቃ አያስፈልገውም! ስህተትን ማንም ይሳሳታል፤ አንተ ግን መዋሸትህን እያወክ እየዋሸህ ነው፡፡ ይህንን በማድረግህ ደግሞ ዛሬህን ብቻ ሳይሆን ነገህንም እያበላሸህ ነው፡፡ ከእንግዲህ ማን ያምንሃል? ማንስ በቁምነገር ይሰማሃል? ውሸታምነትህ በአደባባይ ታይቷል፡፡ Shame! ያሳፍራል!

**ለአምስቱ ጥያቄዎች የሰጣቸው “መልስ”**

መግቢያው ላይ ለቀረቡት የስቅለት ታሪካዊ ማስረጃዎችና በቁርአን ጥቅስ ላይ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ አልሰጠም፤ ሊሰጥም አይችልም ምክንያቱም እስከ ዛሬ ድረስ ምላሽ የሰጠ ሙስሊም የለምና፡፡ ቁርአን ዒሳ አልተሰቀለም አይልም፡፡ ይህንን እኔ ብቻ ሳልሆን ለየሕያ የኩረጃ ምንጭ የሆኑት አሕመዲያዎችም ጭምር የሚናገሩትና እንደ እምነት አቋም የያዙት ነው፡፡

በመግቢያው ላይ የሚገኙትን ነጥቦች በመዝለል በቀጥታ ወደ ዝርዝር ጥያቄዎቹ ነው የገባው፡፡ ከ1-5 ላሉት ብቻ መልስ ለመስጠት ወደ 40 የሚጠጋ ደቂቃ የወሰደ ሲሆን ከዚህ በኋላ ስንት ኦዲዮዎችን በመልቀቅ ጊዜያችንን በከንቱ ለማባከን እንዳቀደ አላውቅም፡፡ እስኪ መልስ ያላቸውን እንያቸው፡-

1. አይሁድ ኢየሱስን ለመግደል መፈለጋቸውን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነው ያየው፡፡ እርሱም “በአደባባይ ሰቅሎ ያልተሳካለት መሲህ መሆኑን ማረጋገጥ” የሚል ነው፡፡ ይህ ከግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚገባው ብቸኛው ጉዳይ አይደለም፡፡
    - ሲጀመር አይሁድ ኢየሱስን መግደል ይፈልጉ ነበር፤ ለመግደልም በተደጋጋሚ ሞክረዋል፡፡ በዚህም ይሁን በዚያ ግባቸው እርሱን መግደል ነበር፡፡ “ያልተሳተሳካለት መሲህ መሆኑን ማረጋገጥ” የሚለው በአደባባይ እንዲሞት ከመፈለጋቸው በመነሳት የተሰጠ አስተያየት ነው፡፡ ሆኖም በግልፅም በስውርም የመግደል ሙከራዎችን ማድረጋቸውን ስንመለከት ዋና ዓላማቸው እርሱን በመግደል ማስወገድ መሆኑን እናስተውላለን፡፡ ስለዚህ “ያልተሳካለት መሲህ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነው” ብሎ ሙጭጭ ማለት አያስኬድም፡፡

- በመጀመርያው ክፍለ ዘመን አይሁድ የሮም ቅኝ ተገዢዎች ስለነበሩ ያለ ሮማውያን የፍርድ ሒደት ሰዎችን መግደል አይችሉም ነበር (ምናልባት ጥቂት ጉዳዮች ቢኖሩም የኢየሱስን ሁኔታ አይመለከቱም)፡፡ *"ጲላጦስም፦ እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት አላቸው። አይሁድም፦ **ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም** አሉት፡፡" (ዮሐ. 18፡31)* ስለዚህ ኢየሱስን የሚያህል በምድረ እስራኤል የታወቀ ሰው ያለ ትክክለኛ የፍርድ ሒደት ማስገደል መጥፎ ውጤት ይኖረዋል፡፡ የአይሁድ መሪዎች ዘግይተውም ቢሆን ይህንን አላገናዘቡም ማለት አይቻልም፡፡
- በመጀመርያው ክፍለ ዘመን አይሁድ የዳዊት መሲህ እና ካህን መሲህ (የዮሴፍ ልጅ) ሲጠብቁ ነበር (Davidic Messiah and Priestly Messiah)፡፡ የዳዊት መሲህ ጦረኛና ድል አድራጊ ሲሆን ካህን መሲህ ግን ይሸነፋል፣ መከራን ይቀበላል፤ ይሞታል፡፡ በዚያ ዘመን የነበሩት አይሁድ ሁለት ዓይነት መሲሆችን ሲጠብቁ የነበሩት መሲሁ መከራን እንደሚቀበልና ደግሞም ጠላቶቹን ድል እንደሚነሳ በብሉይ ኪዳን የተነገረውን ተቃራኒ የሚመስል ሐሳብ ማስታረቅ ስለተሳናቸው ነበር https://www.chaim.org/2messiah.htm፡፡ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ሁለቱንም መሲሃዊ ሚናዎች እንደሚጫወትና መጀመርያ መከራ መቀበሉን በመጨረሻው ዘመን ደግሞ ጠላቶቹን ድል ለመንሳት መመለሱን ስለሚያምኑ ሁለቱ ትንቢቶች አይጋጩባቸውም፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ መሞቱ በዚያን ዘመን በነበረው የአይሁድ እምነት መሠረት እንኳ የዳዊት መሲህ አለመሆኑን እንጂ ካህናዊ መሲህ (የዮሴፍ ልጅ) አለመሆኑን ስለማያረጋግጥ መሞቱ የአይሁድ መሪዎችን ዓላማ አፅድቋል ማለት አይቻልም፤ ስለዚህ የሕያ ተሳስቷል፡፡
- ኢየሱስ ሰዓቱ ሲደርስ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን የገለፅኩ ቢሆንም የሕያ ግን ኢየሱስ በመጨረሻዋ ሰዓት ከመከራ ይድን ዘንድ መጸለዩን በመጥቀስ ኢየሱስ ራሱን አሳልፎ አልሰጠም ይለናል፡፡ መልሴን ጨርሶ አለማንበቡ ግልፅ ነው፡፡ ኢየሱስ የጭንቀት ጸሎት ለምን እንደጸለየ ጥያቄ ቁጥር 7 እና 30 ላይ በቂ ምላሽ ሰጥቻለሁ፡፡ በገዛ ፈቃዱ የሚመጣበትን እያወቀ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ፣ እንደሚሞት በግልፅ ለሐዋርያቱ ነግሮ፣ ሊይዙት ሲመጡም "እኔ ነኝ" ብሎ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ብዙ ጥቅሶችን በመጥቀስ አስረድቻለሁ፡፡ (ለጥያቄ ቁጥር 3፣ 4፣ 5፣ 6 እና 29 የተሰጠውን መልስ ተመልከቱ፡፡) የነፃነት ታጋዮችን ጀግንነት ከክርስቶስ ጭንቀት ጋር በማነፃፀር ለተናገረው ደግሞ በቁጥር 29 ሁለተኛው ነጥብ ላይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ አደራ እንደ የሕያ እየዘለላችሁ አታንብቡ፤ ጨርሳችሁ አንብቡ፡፡
- የጠቀስኳቸውን ትንቢቶች አይሁድ ለኢየሱስ እንደተተነበየ አለማመናቸውን በመግለፅ መሞቱ መሲህ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ለጻፍኩት ምላሽ አይሁድ ትንቢቶቹ ለመሲሁ እንደተነገሩ እንደማያምኑ በመግለፅ መልስ ለመስጠት ሞክሯል፡፡ ዳሩ ግን ዋናው ነጥብ የአይሁድ ትንቢቶቹን ማመን አለማመን ሳይሆን ትንቢቶቹ ስለ ኢየሱስ የተነገሩ ግልፅ ትንቢቶች መሆናቸው ነው፡፡

ትንቢቶቹ ስለ ኢየሱስ አይናገሩም የሚል ካለ መነጋገር ይቻላል፡፡ ነገር ግን አይሁድ አያምኑምና ስለ ኢየሱስ አይደለም የሚል አመክንዮ ገለባ ነው፡፡ ሲቀጥል ደግሞ አይሁድ አይቀበሉም ሲባል የጅምላ ንግግር ከሆነ ሐሰት ነው፡፡ ትንቢቶቹ ለኢየሱስ መሆናቸውን ተቀብለው የነገሩን የመጀመርያዎቹ ሰዎች አይሁድ ነበሩ፡፡ ሁሉም የኢየሱስ ሐዋርያትና የመጀመርያዎቹ ክርስቲያኖች አይሁድ ነበሩ፡፡ ኋላም ቤተክርስቲያን ሰፍታ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ክርስቲያኖች አይሁድን መግፋት እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ ብዙ ሺህ ክርስቲያን አይሁድ ነበሩ፡፡ በዚህ ዘመንም ቢሆን ትንቢቶቹ ስለ ኢየሱስ መሆናቸውን የተቀበሉ በሞቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ መሲሃዊ አይሁዶች አሉ፡፡ የታልሙድ ጽሑፎችና የሙት ባሕር ብራናዎችም ትንቢቶቹ ለመሲሁ የተነገሩ መሆናቸውን በማረጋገጥ "አይሁድ አይቀበሉም" የሚለውን የጅምላ ፍረጃ ውድቅ ያደርጋሉ፡፡ ጉዳዩ በጣም ሰፊ ነው፤ የሕያ ግን በቁንፅል ዕውቀት እያወራ ነው፡፡

- ሬዛ አስላን (Raza Aslan) የተባለ ሰው ስለ ኢየሱስ የጻፈውን መጽሐፍ ጠቅሶ "ኢየሱስን ያልተሳካለት መሲህ ይለዋል" ብሎ የእርሱን አባባል ዋቢ ማድረጉ ከማስገረም አልፎ የሚያስቅ ነው፡፡ Failed Messiah የምትለዋን ቃል የደጋገማት የሬዛ አስላንን የተረት መጽሐፍ ስላነበበ ነው ማለት ነው፡፡ ሲጀመር ሬዛ አስላን የታሪክ ምሑር ሳይሆን የፈጠራ ጽሑፎች ፕሮፌሰር ነው፡፡ መጽሐፉም የፈጠራ ጽሑፍ እንጂ ስለ ኢየሱስ ታሪክ እንደ ልሒቃዊ መጽሐፍ ሊጠቀስ የሚበቃ አይደለም፡፡ የእርሱን መጽሐፍ እንደ ተዓማኒ ምንጭ ጠቅሶ የጻፈ አንድም ሊቅ መኖሩን የሕያ ሊያሳየን አይችልም፡፡ ሁለተኛው ሬዛ አስላን ሙስሊም ነው፤ ሆኖም ግን በኢየሱስ መሰቀልና መሞት ያምናል፡፡ ይህም ቁርአን ስለ ኢየሱስ ስቅለትና ሞት የተናገረው ሐሳብ አሻሚና ሙስሊሞችን ለክፍፍል የዳረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡ የሕያ ግን በመግቢያው ላይ "እስልምና የኢየሱስን ስቅለት አስመልክቶ ግልጽ አስተምህሮ ስላለው ከነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የራቀ ነው" በማለት ደስኩሮልናል፡፡ ባዶ ዲስኩር፡፡
- ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን "ተራ ተረት" ብሎታል፡፡ ነገር ግን ይህ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልፅ የሚመሰክሩት እውነታ ነው፣ ለቤተክርስቲያን ምሥረታና ሐዋርያት ነፍሳቸውን ለሞት አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ትንሣኤውን በመመስከር ለመፅናታቸው ብቸኛው አመክንዮአዊ ማብራርያም ነው፡፡ ኢየሱስ ተሰቅሎ፣ ሞቶ፣ በሦስተኛው ቀን መቃብሩ ባዶ ሆኖ ለመገኘቱ የተለያዩ ሰዎች የሚያቀርቧቸውን መላ ምቶች በሙሉ ውድቅ በማድረግ ልቆ የሚታይ በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የበለጸገ ክስተትም ነው፡፡ ከሐዋርያት እምነታቸውን የተቀበሉት የቤተክርስቲያን አበውም በዚህ ዙርያ ከሐዋርያት የሰሙትን ምስክርነት ስለጻፉልን "ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ባሉት ጽሑፎች ውስጥ አይገኝም" የሚለው የየሕያ አባባል ሐሰት ነው፡፡ ክርስቶስ ዛሬም ሕያው ሆኖ የሰዎችን ሕይወት ሲለውጥ መታየቱ ለትንሣኤው ሌላ ማረጋገጫ ነው፡፡ በዚህ ላይ ለመወያየት አቅሙ አለኝ የሚል ሙስሊም ካለ ማስረጃዎችን እያቀረቡ መወያየት ይቻላል፡፡

"ኢየሱስ አልተሰቀለም" የሚል ከታሪክ በተፃራሪ የቆመና በተማሩት ሙስሊሞች እየተተወ የሚገኝ እሳቤን እንደ እምነት አቋም ይዞ የክርስቶስን ትንሣኤ "ተረት ነው" ማለት በእጅጉ የሚያስቅ ንግግር ነው፡፡ "አልተሰቀለም" የሚል ተረት እውነት እንዲሆን የክርስቶስን ሐዋርያት ምስክርነት ማጣጣል ነፍስን ለሐሰት መሸጥ ነው፡፡

2. "ይሰቀል ዘንድ ማን ፈለገ?" ለሚለው ነጥብ የሰጠሁትን ምላሽ በተመለከተ እንደገና ብዙ ስህተቶችን ሰርቷ፡፡

- ሕዝቡ ሁሉ "ይሰቀል" ማለቱን በመጥቀስ የኢየሱስ ተከታዮች ራሳቸው "ያልተሳካለት መሲህ" መሆኑን ተረድተው "ይሰቀል" ሲሉ እንደነበር ነግሮናል፡፡ በወቅቱ በዚያ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል የኢየሱስ ተከታዮች መኖራቸውንና አብረው "ይሰቀል" ስለማለታቸው ምን ማስረጃ ይሰጠናል? ወፍ የለም! ሰውየው ከገዛ ምናቡ እንጂ በማስረጃ እየተናገረ አይደለም፡፡
- የአይሁድ መሪዎች ሕዝቡ የኢየሱስን መሰቀል እንዲጠይቅ ማነሳሳታቸውን በተመለከተ እኔ ለማለት የፈለኩትና የሕያ የተረዳበት መንገድ የተራራቀ ነው፡፡ ኢየሱስ አብዛኛው አገልግሎቱ በገሊላ ስለነበር በገሊላ ብዙ ተከታዮች ነበሩት፤ ለዚህ ነበር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣላቸው ሲጠባበቁ የነበሩት (ዮሐ. 7፡1፣ 7፡25, 11:56-57)፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱ ለአይሁድ መሪዎች ምቹ ቸጋጣሚ ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በኢየሩሳሌም እምብዛም ስላላገለገለ የተከታዮቹ ብዛት እንደ ገሊላ አልነበረም፡፡ ስለዚህ የኢየሩሳሌም ሕዝብ የኢየሱስን መሰቀል እንዲጠይቅ ማነሳሳት ለእነርሱ ቀላል ነበር፡፡ ተሳክቶላቸዋልም፡፡
- የሕያ `ሕዝቡን አነሳሱት` የሚል ነገር እንደሌለና ይህም የኔ የተሳሳተ መረዳት መሆኑን ተናግሯል፡ ፡ ነገር ግን ይህ በግልፅ የተጻፈ በመሆኑ ስህተቱን በቀላሉ ማሳየት ይቻላል፡-
  - "የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ግን በርባንን እንዲለምኑ <u>ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ</u>።" (ማቴ. 27፡20)
  - "በዚያም በዓል የለመኑትን አንድ እስረኛ ይፈታላቸው ነበር። … ሕዝቡም ወጥተው እንደ ልማዱ ያደርግላቸው ዘንድ እየጮኹ ይለምኑት ጀመር። ጲላጦስም፦ የአይሁድን ንጉሥ እፈታላችሁ ዘንድ ትወዳላችሁን? ብሎ መለሰላቸው፤ የካህናት አለቆች በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና። <u>የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ፈንታ ይፈታላቸው ዘንድ ሕዝቡን አወኩአቸው</u>።" (ማር. 15፡6-11)

ለየሕያ ያለኝ መልእክት ከመናገርህ በፊት አንብብ የሚል ነው፡፡

3. ለጥያቄው ጥቅሶችን እየጠቀስኩ የሰጠሁትን ምላሽ በደፈናው "መልሱ ጭራሽ ከነጥቡ ጋር አይገናኝም፤ አንብቡትና ተረዱት፤ እንዳላረዝምባችሁ" የሚል የሰነፍ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ለማጣጣል ቢሞክርም

የተሰጠውን መልስ መቀልበስ የሚችልበት ማስረጃ የለውም፡፡ ሙግቱ ውድቅ መሆኑን ተቀብሏል ማለት ነው፡፡ አንብቡትና ፍርዱን ስጡ፡፡

4. የኢየሱስ ስቅለት ግድያ ነው መሥዋዕትነት? ለሚለው ቁጥር 32 ላይ መልስ የሰጠሁ ቢሆንም እዚያ መልስ የተሰጣቸውን ነጥቦች ያመነዥጋል፡፡ ይህም ጠቅላላ ጽሑፉን ያገናዘበ ምላሽ ሳይሆን ቅንጭብጫቢ ሐሳቦችን ይዞ ለአሁን ብቻ የምታገለግለውን መውጫ ቀዳዳ ማነፍነፉን ያመለክታል፡፡ እዚያ ላይ እንዲህ ብዬ ነበር፡- "ስቅለት በክፉ ሐሳብ ተነሳስተው ኢየሱስን ከገደሉት ከሮማውያንና ከአይሁድ አኳያ ግድያ ነው፤ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አኳያ ግን መሥዋዕትነት ነው፡፡ አይሁድና ሮማውያን የልብ ሐሳባቸው ክፉ ስለነበር ተግባራቸው ክፉና ኢ-ፍትሃዊ ነው፡፡ የአንድ ሰው ሞት ለአንዱ ወገን ለነፃነት የተከፈለ መሥዋዕትነት ተደርጎ ሲቆጠር ለሌላው ወገን ደግሞ የአመፅ ቅጣት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ይህንን የሚወስነው የቆምንበት ቦታና ዕይታችን ነው፡፡ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ደሙን በማፍሰስ ሕዝቡን ለመቤዠት መሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል፤ ስለዚህ ስቅለት ለእርሱ መሥዋዕትነት አለመሆኑን መናገር ትልቅ ቅጥፈት ነው፡፡ ኢየሱስ ሊገድሉት የሚፈልጉትን አይሁድ የወቀሳቸው በክፉና ኢ-ፍትሃዊ አስተሳሰባቸው ምክንያት ነው፡፡ ኢየሱስን ለመግደል ይፈልጉ የነበሩት ዓለምን ለማዳን በበጎ ሐሳብ ሳይሆን እርሱን ለማጥፋት በክፉ ሐሳብ በመሆኑ ወቀሳው ትክክል ነው፡፡"

ስለዚህ በአራተኛው ቁጥር ላይ ክርስቲያኖች ስቅለት ለኃጢአታቸው መስተሠርያ እንደሆነ ማመናቸውንና ኢየሱስ ግን ግድያ መሆኑን ማመኑን በመግለፅ ሁለቱን ለማጋጨት በመሞከሩ ስህተት መሆኑን ነው የገለፅኩት፡፡ የእርሱ ስህተት የክርስቲያኖችና የኢየሱስ አመለካከት የተለያየ መሆኑን መናገሩ ነው፡፡ ኢየሱስ ስቅለት መሥዋዕት መሆኑን ያምን እንደነበር በተደጋጋሚ ተናግሯል፡፡ ለምሳሌ፡- *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።" (ዮሐ. 3፡14-16) ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።" (ማርቆስ 14፡22-24)፡፡* ኢየሱስ እንዲህ በግልፅ ስቅለት መሥዋዕት መሆኑን ተናግሮ ሳለ ከክርስቲያች ጋር የሚጋጭ አመለካከት እንዳለው መናገር ስህተት ነው፡፡ የኔ ነጥብ እርሱ ነው፡፡ የሕያ ግን ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት እንደሚፈልጉ መናገሩን በመጥቀስ የተሳሳትኩ በማስመሰል የሐሰት ነጋሪት ይደልቃል፡፡ በዮሐንስ 7፡19፣ 8፡37፣ 8፡40 ላይ የጠቀሳቸው ጥቅሶች በስቅለት ወቅት ስለነበረው ሁኔታ ሳይሆን ከስቅለት በፊት አይሁድ እርሱን ለመግደል መፈለጋቸውን የሚያመለክቱ በመሆናቸው ሐሳቡን የሚደግፍ ጥቅስ አላቀረበም፡፡ በነዚህ ቦታዎችም ቢሆን "ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ" በማለት ኢየሱስ የተናገረው የአይሁድን ዓላማ ወይንም የልብ መሻት ለመግለፅ እንጂ የእርሱ ሞት መሥዋዕትነት አለመሆኑን እየተናገረ አይደለም፡፡ ይህንን መረዳት የአንስታይንን አእምሮ አይጠይቅም፡፡

በስቅለት ውስጥ የተሳተፉት ወገኖች ተግባራቸው ለምን እንደሚያስጠይቃቸው በቁጥር 38 እና 42 ላይ ምላሽ ሰጥቻለሁ፡፡ የሕያ ስላላነበበ ወይንም አንብቦ ስላልተረዳ እንደጂ ቁጥር 38 ላይ እንዲህ ብያለሁ፡-

“የአንድ ሰው ምግባር ጥሩነት የሚለካው በውጤቱ ብቻ ሳይኾን በፍላጎትና በዓላማውም ጭምር ነው፡፡ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ሲሰጠው በኢየሱስ ላይ ክህደትን በመፈፀም ገንዘብ ለማትረፍ እንጂ የኢየሱስን ተልዕኮ ከግብ በማድረስ ዓለምን ለማዳን አልነበረም፡፡ ይሁዳ ለክፋት ያሰበውን እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅዱን ለማስፈፀም መጠቀሙ ይሁዳን ከወንጀሉ ነፃ አያደርገውም፡፡ የጠያቂው አመክንዮ ትክክል ከሆነ በየዘመናቱ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች በመግደልና በማስገደል ለተሻለው የሰማዕትነት ክብር እንዲበቁ ምክንያት የሆኑ ክፉ ሰዎች ኹሉ ሊሸለሙ ይገባል ማለት ነው፡፡ ለምን ቢሉ እነዚያ ሰዎች ባይገድሏቸውና ባያስገድሏቸው ኖሮ ለሰማዕትነት ክብር በሙብቃት የተሻለውን ሽልማት ባልተቀበሉ ነበር፡፡ ይህ ሙግት መሠረታዊ የማመዛዘን ችሎታ ካለው ሰው አይጠበቅም፡፡ የወደቀ ሙግት ነው፡፡ ገለባ ነው! (ለአሕመዲን ጀበል ከተሰጠው መልስ የተወሰደ)፡፡”

ቁጥር 42 ላይ ደግሞ እንዲህ ብያለሁ፡- “የአንድ ሰው ምግባር ጥሩነት የሚለካው በውጤቱ ብቻ ሳይሆን በፍላጎትና ዓላማውም ጭምር ነው፡፡ ይሁዳ በገንዘብ ወዳድነት፣ አይሁድ በቅንዓት፣ ሮማውያን ደግሞ ለሥልጣናቸው ሲሉ የፈፀሙትን ተግባር እግዚአብሔር በሉኣላዊ ሥልጣኑ ለበጎ መጠቀሙ እነዚህን ወገኖች ከወንጀሉ ነፃ አያወጣቸውም”

ስለዚህ የሕያ ለመፈላሰፍ ከመሞከርህ በፊት አስብ፣ አመዛዝን፡፡

5. አምስተኛውን ምላሽ “መልሱ ያስቃል” አለ፡፡ ጥያቄው በአጭሩ “ኢየሱስ ለምን ነበር ሲደበቅ የነበረው?” የሚል ነው፡፡ መልሱም ግልፅና ቀጥተኛ ነው “ለሁሉ ጊዜ አለው” የሚል፡፡ ትክክለኛ መልስ ነው፡፡ የሕያም አውቆታል፡፡ መልሱን ካነበበ በኋላ ከው አለ፤ ከዚያም ተንተባተበ፤ አንድ ሐሳብ ጀመረና ምን ለማለት እንደፈለገ ሳያስረዳ የኔን ምላሽ ማንበቡን ቀጠለ፡፡ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ሲያዝ ፈርተው መሸሻቸውንና ኢየሱስን ለመከላከል አለመሞከራቸውን እየደሰኮረ ኢየሱስ ትክክለኛ ሰዎችን እንዳልመረጠ ሊያስረዳን ብዙ ተናገረ፡፡ በመጀመርያ ኢየሱስ አብዛኞቹ ዓሣ አጥማጆች የነበሩትን ሰዎች እንጂ ተዋጊ ወታደሮችን አልመለመለም፤ ወታደራዊ ሥልጠናም አልሰጣቸውም፡፡ ሆኖም ኢየሱስን ለመከላከል የተቻላቸውን አድርገዋል፡፡ እንዲህ ተጽፏል፡-

> “በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ፡- <u>ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት። ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው።</u> ኢየሱስ ግን መልሶ፦ ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው።” (ሉቃስ 22፡49-51)
>
> “እነሆም፥ <u>ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ጆሮውን ቈረጠው።</u> በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን? እንዲህ ከሆነስ፦ እንደዚህ ሊሆን ይገባል የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ?” (ማቴዎስ 26፡51-54)

ሐዋርያቱ አቅም ባይኖራቸውም ለመፋለም ቆርጠው ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከለከላቸው፡፡ ከዚያ አካባቢ እንዲሄዱም ምልክት ሰጣቸው፡-

> “ኢየሱስ መልሶ፦ እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ፡፡” (ዮሐንስ 18፡8)

ሐዋርያት የተቻላቸውን ቢያደርጉም ሰዎች ስለነበሩ በዚያች አስጨናቂ ሰዓት ድካም ታይቶባቸዋል፡፡ ነገር ግን ከኢየሱስ አልራቁም ነበር፡፡ በኢየሱስ ስቅለት ወቅት እናቱ ማርያም፣ አክስቱ፣ የሮማዊው ባለሥልጣን የቀለዮጳ ሚስት ማርያም፣ መግደላዊት ማርያም፣ ሰሎሜ፣ የዮሐንስና የያዕቆብ እናት እንዲሁም ከገሊላ ጀምረው የተከተሉት ሌሎች ብዙ ሴቶች በቦታው ነበሩ (ዮሐ. 19፡25-26፣ ማቴዎስ 27፡55-56፣ ማርቆስ 15፡40-41፣ ሉቃስ 23፡49)፡፡ ዮሐንስ እስከ መጨረሻው በቦታው ላይ በመኾን ሞቱን እንደተመለከተ ተጽፏል (ዮሐ. 19፡35)፡፡ ሐዋርያት ኹሉ ጥለውት እንደሸሹ ማቴዎስ 26፡56 ላይ የተጻፈ ቢሆንም ወዲያው ግን ጴጥሮስ ተመልሶ መምጣቱንና የፍርድ ሂደቱን መከታተሉን በቁጥር 58 ላይ እናነባለን፡-

> “ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ሩቅ ኾኖ ተከተለው፥ የነገሩንም ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ውስጥ ገብቶ ከሎሌዎቹ ጋር ተቀመጠ፡፡”

ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ ከታወቀ ከሌላ ደቀ መዝሙር ጋር ተመልሶ እንደመጣና ደቀ መዝሙሩ አስፈቅዶ አብረው ኢየሱስ ለፍርድ ወደቀረበበት የሊቀ ካህናቱ ግቢ እንደገቡ ዮሐንስ ይነግረናል (ዮሐ. 18፡15-16)፡፡ ሐዋርያቱ እንዳይገደሉ በመፍራት ራሳቸውን ባይገልጡም ነገር ግን ኹኔታውን በቅርብ ርቀት ይከታተሉ እደነበር እንገነዘባለን፡፡

ከትንሣኤው በኋላ ግን ታሪክ ተለወጠ፡፡ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም አደባባዮች፣ በቤተመቅደሱ ውስጥና ከዚያም አልፈው በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እየተዘዋወሩ የክርስቶስን ትንሣኤ አውጀዋል (የሐዋርያት ሥራ 2፣ 4፣ 8፣ ወዘተ.)፡፡ በአስቆሮቱ ይሁዳ ቦታ የተተካውን ማቲያስን ጨምሮ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል የተፈጥሮ ሞት የሞተው ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ሲሆን ሌሎቹ ግን ስለ እምነታቸው መሥዋዕት በመሆን አልፈዋል፡፡ በቅፅበት እንዲለወጡ ያደረጋቸው ምንድነው? ከክርስቶስ ትንሣኤ በስተቀር አጥጋቢ ማብራርያ ሊሆን የሚችል ምንም ነገር የለም!

አንድ ነቢይ ነኝ ባይ ከ600 ዓመታት በኋላ ወደ ዋሻ ገብቶ በመውጣት መልአክ ተገለጠልኝ በሚል ቅዠት ይህንን ሐቅ መለወጥ አይችልም! ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሲል ሞቶ ከሙታን ተነስቷል! ስሙ ከዘላለም እስከ ዘላለም የተመሰገነ ይሁን!